# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ!
አባዝተው ያሰራጩ፡
ቁጥር 92 የካቲት 11 2002


# ልዩ እትም

## በሶስት ተከታታይ አገዛዞች በመከላከያ ሠራዊት ከፍተኛ የአዛዥነት ቦታዎች የብሄረሰብ ተዋጽዎ ንጽጽር ጥናት ውጤት

በወያኔ የመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ባሉ ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች ላይ ስለተኮፈሱ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የብሄረሰብ ተዋጽኦ የግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ያደረገውን ጥናት ውጤት ግንቦት 18 2001 ዓ. ም. ለሕዝብ ይፋ ማድረጉ ይታወቃል። የዚያ ጥናት ውጤት አስደንጋጭ ነበር።

ጥናቱ የኤታማዦር ሹምነቱን ጨምሮ በመከላከያ ውስጥ የሚገኙ ሰባት ቁልፍ ቦታዎች ሙሉ በሙሉ የወያኔ አባላት በሆኑ የትግራይ ተወላጆች የተያዙ መሆናቸው ይፋ አደረገ። በመላ ሃገሪቱ ውስጥ ካሉት 61 ቁልፍ የመከላከያ ኃላፊነቶች 58ቱ በትግሬ ብሄረሰብ አባላት የተያዙ መሆኑን ስም ዝርዝራቸውን በማውጣት አጋለጠ። ከዚህም በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሱትን 61 ከፍተኛ ቁልፍ ኃላፊነቶችን ከሚመሩት መካከል ሃያ አምስቱ ጄነራሎች ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ሃያ ሁለቱ ትግሬዎች፣ ሁለቱ አማራዎችና አንዱ አገው መሆናቸው ተገለፀ። ለይስሙላ የገቡትም አንድ የአገውና ሁለቱ የአማራ ተወላጆች በተሾሙበት ቦታም እውነተኛው ሥልጣን ምክትሎቻቸው ሆነው በተቀመጡ የትግራይ ተወላጅ የወያኔ አባላት እጅ ውስጥ መሆኑን አጋለጠ።

- የብሄር ጭቆናን ለማጥፋት ተነስቼ ታግዬ የብሄር፣ ብሄረሰቦች እኩልነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን መሠረትኩ እያለ ወያኔ ነጋ ጠባ ቢለፈልፍም፣
- ህገመንግሥቱ ሉዓላዊ የመንግሥት ሥልጣን በዘር በተደራጁ የክልል መንግሥታት እጅ ውስጥ ነው፤ ፌደራላዊት ኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በፈቃዳቸው ከሥልጣናቸው ቆርሰው በመስጠት የፈጠሯት ነች እያለ ፈጽሞ ሆኖ ስለማያውቅ ነገር ቢዘላብድም፣
- በሰንደቅ ዓላማችን መሃል ላይ የተለጠፈው አርማ የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት መገለጫ ነውና እሱን መቃወም የብሄር ብሄረሰቦችን እኩልነት መፃረር ነው እያለ ቢያደነቁረንም፣
- የብሄር ብሄረሰቦች ቀን የሚባል ብሄራዊ በዓል አውጆ የአገር ባህል ዘፈኖችን ቢያቀርብልንም

በተግባር ግን የእኩልነት ጉዳይ የወያኔ አጀንዳም ፍላጎትም ሆኖ እንደማያውቅ ለኢትዮጵያዊያን ከጥናቱ በፊትም ግልፅ ነበር። በዘር ላይ የተመሠረተ መድልዎ በዘመነ ወያኔ በከፍተኛ ሁኔታ ማገርሸቱ በየእለቱ የሚታይ ሃቅ በመሆኑ ፕሮፖጋንዳው እውነቱን መደበቅ አልቻለም ነበር።

ያም ሆኖ ግን በሕዝብ ብዛት ከ6% የማይበለጠው የትግራይ ህዝብ ድርሻ ከ95% በላይ ይሆናል ብሎ የገመተ የነበረ አይመስልም። በተለይም በሕዝብ ብዛት ከሁሉም የሚበልጠው የኦሮሞ ብሄር ድርሻ 0% ይሆናል ብሎ ማሰብም አይቻልም። በዚህም ምክንያት የጥናቱ ውጤት ወያኔን ለሚያውቁት ጭምር አስደንጋጭ ነበር።

የጥናቱ ውጤት ይፋ ከሆነ ወዲህ

- ለመሆኑ ኢትዮጵያ የማን ነች?
- ኦሮሞ፣ አማራ፣ ሶማሊ፣ ሲዳማ፣ ከምባታ፣ አፋር፣ ጉራጌና ሌሎች ዘውጎች ኢትዮጵያዊያን አይደሉምን?
- ከትግራይ ውጭ ወታደራዊ ሙያና ክህሎት ያለው ሊገኝ አልቻለም?
- የትግራይን የበላይነት ለማስፈን በሚጥሩ የህወአት ስብስቦችና በሌሎቻችን መካከል ያለው ግኑኝነት ምንድነው? ጌታና ሎሌ ወይስ ቅኝ ገዢና ተገዥ?
- ወያኔ ለትግራይ ሕዝብ ምኑ ነው? በዚህ ያፈጠጠ ኢፍትሃዊነት የትግራይ ሕዝብ ምን ይሰማዋል? እውን ወያኔ ትግራይን ይወክላል?
- ይህ ዘረኝነት የት ያደርሰናል?

የሚሉና የመሳሰሉ በአዕምሮ ውስጥ ጭንቀትን የሚፈጥሩ ጥያቄዎች ሲነሱ ቆይተዋል።

እውነቱን ለመናገር በዚህ መረን ያጣ የወያኔ ዘረኛ አደረጃደት ያልበገነ ኢትዮጵያዊ አለ ብሎ ማሰብ ይከብዳል። ሃቁ ፈጦ ሲታይ የወያኔ ሸሪኮች የሆኑ አገራት ዲፕሎማቶችም በአደባባይ ስለኢፍትሃዊ የስልጣን ክፍፍል ደፍረው መናገር ጀመሩ።

ይህም ሆኖ ግን በተለመደ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት "ጉዳችን እንደብቀው፤ ትንሽ አበዙት እንጂ በደል ድሮም የነበረ ነውና እንቻለው" በማለት ሃቁ እንዲደባበስ የመረጡ ኢትዮጵያዊያን ነበሩ፤ አሁንም አሉ። አንዳንዶችም የዚህ ግፍ በይፋ መነገር ብሶትን አስገንፍሎ የማንቆጣጠረው ችግር ውስጥ ያስገባል ብሎ በመፍራት መሸፋፈኑን የመረጡ ነበሩ፤ አሉምም።

በደል ምንም እንኳን እንዲህ እንደ አሁኑ የባሰበት ባይሆንም ድሮም የነበረ መሆኑ አሌ አይባልም። ይህ ማለት ግን አንድ በደል በሌላ በደል ይካሳል ማለት አይደለም። ወያኔም ቢሆም "ድሮ ለደረሰብኝ በደል ካሣ አሁን ተራዬን ሌሎችን መበደል መብቴ ነው " ብሎ ቢያንስ በአደባባይ ነግሮን አያውቅም። በግልባጩ ነጋ ጠባ የሚነገረን እኩል መሆናችንን ነው። በቀድሞ ሥርዓት የተበደለ በአዲሱ ሥርዓት በዳይ ሆኖ ቢገኝ ጥፋቱን አቅልሎ ማየት፤ የሥርዓት ለውጥ የበዳይና ተበዳይ ቦታ መለዋወጥ አድርጎ ከመገነዘብ የሚመጣ እጅግ አደገኛ የሆነ አመለካከት ነው ብለን እናምናለን። በእኛ እምነት የመከላከያ ሠራዊት በዋናነት በብቃት ላይ መመሥራት አለበት። ብቃት ደግሞ በዘር ይገኛል ብለን አናምንም። የችግሩ በይፋ መነገር እማንቆጣጠረው ብሄራዊ አደጋ ውስጥ ይከተናል ለሚሉ ወገኖቻችን – *ሥጋታችሁ ይገባናል። ሆኖም ዛሬ ሸፋፍነን ብናልፈው ነገ እሳተ ገሞራ ሆኖ ያጠፋናል። ይልቁንስ ለአገራችንና ለሁላችንም ደህንነት ሲባል ከአሁኑ ጊዜ ሳነሰጥ ችግሩን እንጋፈጠው –* ስንል ቆይተናል።

እነዚህ ክርክሮች የግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የጥናትና ምርምር ቡድን በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ጥናት እንዲያደርግ ገፋፋው።

በዚህም መሠረት ቡድኑ ከወያኔ በፊት በነበሩ ሁለት አገዛዞች የኢትዮጵያ ሠራዊት የብሄረሰብ ስብጥር ምን ይመስል እንደነበር ለማወቅ የበርካታ ሰዎችን ተሳትፎ የጠየቀ ጥናት አካሂዶ ያገኘውን ውጤት እነሆ ዛሬ ያቀርባል።

ቡድኑ በመጀመሪያው ጥናቱ ለወያኔ ሹማምንት እንዳደረገው ሁሉ የአፄ ኃይለሥላሴንም የደርግንም የጦር ሹማምንት ስም ከብሄር/ብሄረሰብ ጋር ያቀረበው ዝርዝር ዛሬ ይፋ ሆኗል።

ከሁሉ አስቀድሞ  ስለ ጥናቱ ሶስት  መሠረታዊ ነገሮችን ማንሳት ያስፈልጋል::

1. በቀድሞ አገዛዞች ዘር ለቅጥር መስፈርት ሆኖ  አያውቅም፤ በቅጥር ፎርም ላይም አይሞላም ነበር:: ስለሆነም በዚያ ወቅት የነበረ የተዛባ የብሄረሰብ ስብጥር ታቅዶ የተደረገ የፓሊሲ ውሳኔ አድርጎ መውሰድ ተገቢ አይሆንም:: የሆነ ሆኖ ግን የእኩልነት አለመኖር ለወያኔም ለሌሎችም የፓለቲካ ኃይሎች መነሳት እንደአንዱ ምክንያት ተደርጎ ሲቆጠር ቆይቷል። የዚህ ጥናት ውጤት ያ አመለካከት ትክክል ነበርን ብለን እንድንጠይቅ ያስገድደናል።
2. ወያኔ በሥልጣን ዘመኔ አመጣሁ ብሎ ከሚኩራራባቸው ነገሮች አንዱ "የብሄር/ብሄረሰቦችን እኩልነት ነው። ይህ ጥናት በዚህ ረገድ የኋልዮሽ እንጂ ወደፊት እንዳልተራመድን በማያሻማ ሁኔታ ያረጋግጣል።
3. ይህ ጥናት በሜጀር ጄኔራል ማዕርግና ከዚያ በላይ ያሉትን ብቻ ይመለከታል:: በዚህ ጥናት ክፍል ሁለት ከዚያ በታች ያሉት ሹመቶችን ለመዳሰስ ጥረት እናደርጋለን

የሶስቱን አገዛዞች ሰንጠረዦች ጎንለጎን አስቀምጦ ላስተያየ በዘመነ ወያኔ ምን ያህል የኋልዮሽ እንደተጓዝን፤ ዛሬ የቱን ያህል አደጋ ውስጥ እንዳለን መገንዘብ ይችላል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሰንጠረዦቹን በጥንቃቄ እንዲመረምር እየጋበዝን በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ጥቂት ማለት እንሻለን።

1. በሠራዊታቸው ከፍተኛ አመራሮች ውስጥ በነበረው የብሄረሰብ ስብጥር አኳያ አፄ ኃይለ ሥላሴና ደርግ ከወያኔ በእጅጉ የተሻሉ ነበሩ። በንጉሡም ሆነ በደርግ ዘመን ኢፍትሃዊ የስልጣን ክፍፍል

እንደነበረ መከራከር ቢቻልም እንዳሁኑ ዘግናኝ ግን አልነበረም። ይህንን ሃቅ ቀጥሎ ካለው የማጠቃለያ ሰንጠረዥ መረዳት ይቻላል።

| ብሄር/ ብሄረሰብ | ከከፍተኛ ሹማምንት በመቶኛ | | |
|---|---|---|---|
| | በንጉሡ | በደርግ | በወያኔ |
| ኦሮሞ | 13.3 | 25.0 | ምንም |
| አማራ | 55.5 | 45.0 | 4.9 (አማራና አገው) |
| ትግሬ* | 11.1 | 2.5 | 95.1 |
| ጉራጌ | 4.4 | 5.0 | ምንም |
| ወላይታ | | 2.5 | ምንም |
| ሃረሪ | | 2.5 | ምንም |
| ድብልቅ | 15.5 | 17.5 | ምንም |
| ድምር | 99.8 | 100 | 100 |

*በንጉሡና በደርግ ጊዜዓት "ትግሬ" ዛሬ በኤርትራ ያለውንም ትግርኛ ተናጋሪ ያጠቃልላል

2. በጦር ውስጥ በነበረው የብሄረሰብ ስብጥር ረገድ ደርግ ከንጉሡ የተሻለ እንደነበረ የጥናታችን ውጤት ያረጋግጣል። ደርግ ቀድሞ ያልነበሩ ወላይታና ሃረሪን ወደ ኃላፊነት አምጥቷል። የአማራውን ድርሻ በመቀነስ የኦሮሞን አሳድጓል። የድብልቁንም መጠን በመጨመር ከሞላጎደል ሠራዊቱ ከአናቱ ጀምሮ ኢትዮጵያን ለማስመሰል ጥሯል። በወያኔ ዘመን ግን የሠራዊቱ አመራረ ኢትዮጵያን ፈጽሞ አይመስልም።
3. በንጉሡና በደርግ ዘመን በሠራዊቱ የአማራው በተለይም የሸዋ አማራ የበላይነት እጅግ የጎላ ተደርጎ ሲቀርብ የነበረው የተጋነነ መሆኑ አንዱ የዚህ ጥናት ያልተጠበቀ ውጤት ነው።
4. በንጉሡም ሆነ በደርግ ጊዜ የነበሩ ከፍተኛ መኮንኖች ዘመናዊ ሥልጠና ያገኙና አብዛኛዎቹ ደረጃ ጠብቀው በማደግ ለከፍተኛ ማዕረግ የበቁ ነበሩ። በአንፃሩ የወያኔ መኮንኖች ዘመናዊ የውትድርና ትምህትን ያልቀመሱ የልምድ ተዋጊዎችና አዋጊዎች የነበሩ ናቸው። የወያኔ የሹመት አሰጣጥም እርከን የጠበቀ አይደለም።
5. በቀደሙት አገዛዞች ምክትሉ ወይም ከዚያ ያነሰው አዛዡን የሚያዝበት ሁኔታ አልነበረም ማለት ይቻላል። በተወሰነ መጠን በደርግ ጊዜ የሥልጣን ተዋረድ መፋለስ ቢታይም በፓለቲካ ኮሚሳሮች ምክንያት ፓለቲካዊ ወገንተኝነት ላይ ያተኮረ እንጂ ዘርን መሰረት ያደረገ አልነበረም። ዛሬ በዘመነ ወያኔ ሥልጣን በዘር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ማዕረግ ተሰጧቸው ሥልጣን ግን የሌላቸው ከትግራይ ብሄር ውጭ የሆኑ አሻንጉሊት መኮንኖችን ጥቂትም ቢሆን ማግኘት ይቻላል።

**የዚህ ጥናት እንድምታው ምንድነው?**

አደጋ ውስጥ ነን። ይህ ጥናት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን የገጠመን አደጋ ምን ያህል ግዙፍ እንደሆነ ያሳየናል። በእውነቱ አገር አለን? ይህንን እያየን ዝም ካልን ኢትዮጵያዊያን ነን ማለት እንችላለን?

እንዲህ ዓይነቱ ዘረኛ የሠራዊት አደረጃት በፓለቲካ፣ በማዕበራዊ ኑሮዓችንና በኢኮኖሚያችን ላይ ስለሚኖረው ተጽዕኖ ማጥናት ይገባል። ይህን ለግል ተመራማሪዎች እንተወው።

**የእኛ ዋነኛ መልዕክት ግን አጭር ነው።**

እኛ በግንቦት 7 ሥር የተሰባሰብን ኢትዮጵያዊያን "በቃ!!!! መሮናል!!! ይህን ብካይ ሥርዓት በቶሎ ካላስወገድን አገር ስለማይኖረን ቆርጠን ተነስተናል!!!" ብለናል

**እርስዎስ? እናንተስ???**

## የደርግ፣ በኋላም የኢሕድሪ መከላከያ ሠራዊት የምድር፣ የአየርና የባህር ኃይሎችና የፖሊስ ሠራዊት ከፍተኛ ሹማምንት

| ተ/ቁ | ሙሉ ስም | ማዕረግ | ይዘውት የነበረው ከፍተኛው ሥልጣን | ዘውግ/ የትውልድ ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተስፋዮ ገብረኪዳን | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የመከላከያ ሚኒስትር | ኦሮሞ (ከሸዋ ሰላሌ ኦሮሞዎች ወላጆች ተወልደው ሃረር ያደጉ) | የደርግ ቋሚ ኮሚቴና የኢሠፓ የፓለቲካ ቢኦ አባል ከማንም በላይ ኃይልና ሥልጣን የነበራቸው በ1991 የአንድ ሣምንት ፐሬዚዳንት |
| 2 | ኃይለጊዮርጊስ ሃብተማርያም | ሜጀር ጄኔራል (የክብዘበኛ 2ኛ ኮርስ) | የመከላከያ ሚኒስትር | የሸዋ አማራ | በተስፋዬ ሥር ቺፍ ኦፍስታፍ ነበሩ |
| 3 | መርዕድ ንጉሴ | ሜጀር ጄኔራል (የክብር ዘበኛ 3ኛ ኮርስ) | የአብዮታዊ ጦር ኃይሎች አዛዥ | የሸዋ ኦሮሞ | በ1981 የመፈንቅለ መንቅግሥት ሙከራ መክሸፍ ራሳቸው ያጠፉ |
| 4 | ገብረ ክርስቶ ስ ቡሊ | ብርጋዴር ጄኔራል (ጦርሠራዊት፣ ከሆለታ ) | የብሄራዊ አብዮታዊ ወታደራዊ ዘመቻ አዛዥ | የወለጋ ኦሮሞ | እስከ 1970ቹ አጋማሽ ለደርግ ሊቀመንበር ተጠሪ ሆኖ መላውን ወታደራዊ ዘመቻዎች የመቆጣጠር ከፍተኛ ሥልጣን የተጣለበት የኃላፊነት ቦ ታ ነበር |
| 5 | ኃይሉ ገብሬ ሚካኤል | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት ሆለታ) | የምድር ጦር አዛዥ | ኦሮሞና ጉራጌ (ቅልቅል) | ከመፈንቀለ መንግሥት ሙከራ በመሳተፋቸው  የሞት ፍርድ ተፈፃሚየሆነባቸው |
| 6 | ተስፋዬ ብርሃኑ | ሪር አድሚራል (1ኛ ኮርስ) | የባህር ኃይል አዛዥ | ወላይታ | ከመፈቅለ መንግሥት ሙካራ በኃላ ታስረው የነበሩ |
| 7 | ፋንታ በላይ | ሜጀር ጄኔራል (አየር ኃይል) | የአየር ኃይል አዛዥ | የጎንደር አማራ | በመፈንቀለ መንግሥት ሙከራ በእስር እንዳሉ የተገደሉ |
| 8 | ደምሴ ቡልቶ | ሜጀር ጄኔራል (የክብር ዘበኛ 3 ኛ ኮርስ አየር ወለድ) | የ2ኛው አብዮታዊ ጦር አዛዥ ኤርትራ | የሸዋ ኦሮሞ | ከመፈንቀለ መንግሥት ሙከራ በመሳተፋቸው  አስመራ እያሉ የተገደሉ |
| 9 | አምሃ ደስታ | ሜጀር ጄኔራል (አየር ወለድ) | የአየር ኃይል አዛዥ | የሸዋ አማራ | በ1981 የመፈንቅለ መንቅግሥት ሙከራ መክሸፍ ራሳቸው ያጠፉ |
| 10 | ዘለቀ በየነ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት ሆለታ) | የ4ኛው አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ | አማራ ከወሎ | የደርግአባል፤ የኢሠፓ ማ/ኮሚቴ አባል ከዓመታት የሲቪል ሥራ በኋላ ወደ ውትድርና የተመለሱ |
| 11. | አሥራት ብሩ | ሜጀር ጄኔራል (የክብር ዘበኛ 3ኛ ኮርስ) | የ3ኛ አብዮታዊ ጦር አዛዥ (ትግራይ) | የሸዋ ኦሮሞ | በቅድመ 1983 በተያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ሰርዋል |
| 12. | ሃዲስ ተድላ | ሌተናል ጄኔራል (አየር ኃይል) | ቺፍ ኦፍ ስታፍ | የሸዋ አማራ | የደርግ ቋሚ ኮሚቴ የኢሠፓ ፓሊት ቢሮ አባል። ከዓመታት የሲቪል ሥራ በኋላ ወደ ውትድርና ሙያ የተመለሱ |
| 13. | መስፍን ገብረቃል | ሜጀር ጄኔራል(ጦር ሠራዊት፣ ሀረር አካዳሚ፤ ሳንደርስት) | ም/ ቺፍ ኦፍ ስታፍ ኦፕሬሽንስ | ኤርትራ | የአርበኛ ልጅ እና በመከላከያ የተለያዩ ከፍተኛ ኃላፊነቶች የሰሩ |
| 14. | የኋላእሸት ግርማ | ሪር አድሚራል (ባህር ኃይል) | የባህር ኃይል አዛዥ | አማራና ጉራጌ (ቅልቅል) | የደርግና የኢሠፓ ማ/ኮሚቴ አባል። ከዓመታት የሲቪል ሥራ በኋላ ወደ ውትድርና የተመለሱ |
| 15. | ስዩም መኮንን | ሜጀር ጄኔራል(ጦር ሠራዊት፣ ሆለታ) | ም/ቺፍ ኦፍ ስታፍ ኢንቴል | የሸዋ አማራ | ከመፈቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ ወደ ቺፍ ኦፍስታፍነት ያደጉ |
| 16. | አበበ ወልደማርያም | ሜጀር ጄኔራል (አየር ኃይል) | የሎጂስቲክ ም/ ሚኒስትር | ጉራጌና አማራ (ድብልቅ) | |
| 17. | አለማየሁ አጎናፍር | ሜጀር ጄኔራል (አየር ኃይል) | የአየር ኃይል አባል | የሸዋ አማራ | ከመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ የተሾሙ |
| 18. | እምቢበል አየለ | ሜጀር ጄኔራል(ጦር ሠራዊት፣ ሀረር አካዳሚ፣ 1ኛ ኮርስ) | የምድር ጦር ጠቅላይ አዛዥ | አማራ (ከሀረር) | ከመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ የተሾሙ |
| 19. | ብርሃኑ ጀምበሬ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት፣ ሆለታ) | የ1ኛ አብዮታዊ ሠራዊት አዛዥ | የጎጃም አማራ | |
| 20 | ውብሸት ደሴ | ሜጀር ጄኔራል | የ2ኛ አብዮታዊ | የአርሲ ኦሮሞ | ከመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ሠራዊት | | ወደ ጦሩ የተመለሱ |
| 21. | ከፈለኝ ይብዛ | ሜጀር ጄኔራል (ጦርሠራዊት፣ሆለታ) | የማዕከላዊ እዝ አዛዥ | ሶዶ ጉራጌ | እስከ 1983 በተለያዩ ኃላፊነቶች ሠርተዋል |
| 22. | ጥላሁን አርጋው | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት፣ሆለታ) | የአሰብ ልዩ እዝ አዛዥ | ጉራጌና አማራ (ድብልቅ) | እስከ 1983 |
| 23. | ረጋሳ ጅማ | ሜጀር ጄኔራል (የክብር ዘበኛ 3ኛ ኮርስ) | የ2ኛ አብዮታዊ ጦር አዛዥ | ኦሮሞ (ከኢሉ አባቦራ) | በተያዩ የኃላፊነትቦታዎች ሰርተዋል |
| 24. | ጌታቸው ገዳሙ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት፣ ሆለታ) | የ1ኛ አብዮያዊ ክፍለ ጦር ም/አዛዥ | የጎጃም አማራ | እስከ 1983 የተለያየ ኃላፊነቶች ሰርተዋል |
| 25. | ክንፈ ገብርኤል ድንቁ | ሜጀር ጄኔራል (የክብር ዘበኛ 3ኛ ኮርስ) | የወታደራዊ ኦፕሬሽኖች ኃላፊ | ጉራጌ | በተያዩ የመከላከያ ኃላፊነትቦታዎች ሰርተዋል |
| 26. | ሁሴን አህመድ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት፣ ህረር አካዳሚ 1ኛ ኮርስ) | የ2ኛ አብዮታዊ ጦር ም/ አዛዥ | አማራ (ወሎ) | ወደ ሳውዲ አረቢያ እስከተሰደዱበት 1983 ድረስ በተለያዩ ቦታዎች ሰርተዋል |
| 27 | አለማየሁ አየለ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት፣ ሆለታ) | የምድር ጦር ሎጂስቲክስ ም/ አዛዥ | አማራ | እስከ 1983 |
| 28 | በድሉ ዱኪ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት፣ ሆለታ) | የመከላያ ሎጂስቲክ አዛዥ | የሸዋ ኦሮሞ | እስከ 1983 |
| 29. | ወጋየሁ ጋሻው | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት፣ ሆለታ) | የ2ኛ አብዮታዊ ሠራዊት ም/አዛዥ | አማራና ኦሮሞ (ቅልቅል) | እስከ 1983 በዚህ ኃላፊነት ቆይተዋል |
| 30. | መርዳሳ ለሊሳ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት፣ ሆለታ) | የዘመቻ ቴዎድሮስ (1983) አዛዥ | የሸዋ ኦሮሞ | እስከ 1983 |
| 31. | አበራ አበበ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት፣ ልዩ ኃይል፣ ሆለታ) | የመከላከያ ወታደራዊ ኦፕሬሽን ኃላፊ | የሸዋ ኦሮሞ | ከመፈቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ የተገደሉ |
| 32. | አብዱላሂ ዑመር | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት፣ ሀረር አካዳሚ 1ኛ ኮርስ) | የመከላከያ የሎጂስቲክ ኃላፊ | አደሬ | ከመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ የታሰሩ |
| 33. | ሙላቱ ነጋሽ | ሜጀር ጄኔራል (የክብር ዘበኛ 3ኛ ኮርስ) | የ3ኛ አብዮታዊ ጦር አዛዥ | ድብልቅ | በስደት ላይ የሚገኙ |
| 34. | ቁምላቸው ደጀኔ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት፣ ሆለታ) | የ2ኛ አብዮታዊ ሠራዊት ም/ አዛዥ | የጎጃም አማራ | በመፈቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ በስደት ላይ እያሉ ሕይወታቸው ያለፈ |
| 35. | ወርቁ ዘውዴ | ሜጀር ጄኔራል (ፓሊስ) | የኢትዮጵያ ፓሊስ አዛዥ | አማራ (ከሀረር) | ከመፈቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ የተገደሉ |
| 36. | ዘውዴ ገብረየስ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የኮር አዛዥ | አማራ (ከደቡብ) | ከመፈቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ የተገደሉ |
| 37. | አለማየሁ ደስታ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የምድር ጦር ም/ አዛዥ | የሸዋ አማራ | ከመፈቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ የተገደሉ |
| 38. | ገብረየስ ወልደሃና | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የመከላከራ የፓለቲና ኮሚሳሪያት አዛዥ | የሸዋ አማራ | የደርግና የኢሠፓ ማ/ኮሚቴ አባል። በአውሮፕላን አደጋ የሞቱ |
| 39. | ንጉሴ ወልደሚካኤል | ሜጀር ጄኔራል (ፓሊስ) | የፓሊስ አዛዥ | የጎጃም አማራ | በኋላ ወደ ሲቪል ሥራ ተዛውረዋል |
| 40. | ግርማይ ነዋይ | ሜጀር ጄኔራል(ፖሊስ) | የፓሊስ አዛዥ (ከመፈቅለ መንግሥት በኋላ) | አማራና ጉራጌ (ድብልቅ) | የደርግና የ ኢሠፓ ማ/ኮሚቴ አባል፤ ከመፈቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ ከሲቪል ወደ ፓሊስ ሠራዊት አዛዥነት የተዛወሩ |

## ከፍተኛ የምድር፣ የአየርና የባህር ኃይል እና የፓሊስ ሠራዊት ሹማምንት

| ተ/ቁ | ሙሉ ስም | ማዕረግ | በንጉሡ ጊዜ ይዘውት የነበረው ከፍተኛው ሥልጣን | ዘውግ/ የትውልድ ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ከበደ ገብሬ | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የመከላከያ ሚኒስትር | የሸዋ አማራ | |
| 2 | መርዕድ መንገሻ | ሌ/ጄኔራል | የመከላከያ ሚኒስትር | የሸዋና የጎጃም አማራ | |
| 3 | ኢያሱ መንገሻ | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የንጉሠ ነገሥት ጦር ቺፍ ኦፍ ስታፍ | ትግሬና ኤርትራ | |
| 4 | አቢይ አበበ | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የመከላከያ ሚኒስትር | የሸዋ አማራ | |
| 5 | ኢያሱ ገብረስላሴ | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የምድር ጦር ጠቅላይ አዛዥ | ኤርትራ | |
| 6 | ኃይሌ ባይከዳኝ | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ቺፍ ኦፍ ስታፍ | ትግሬ (አድዋ) እና አማራ (ጎጃም) ድብልቅ | |
| 7 | አበበ ገመዳ | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ አዛዥ | የሸዋ ኦሮሞ | |
| 8 | አሰፋ አያነ | ሌ/ጄኔራል (አየር ኃይል) | የንጉሠ ነገሥቱ የአየር ኃይል አዛዥ | የጎንደር አማራ | |
| 9. | ወልደሥላሴ በረካ | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የንጉሠ ነገሥቱ የምድር ጦር አዛዥ | ጉራጌ | |
| 10 | ደርሴ ዱባለ | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የምድር ጦር አዛዥ | ጉራጌና አማራ ድብልቅ | |
| 11 | ሙሉጌታ ቡሊ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የጦር ኃይሎች አዛዥ (በኋላ የ ማዕበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነዋ) | የወለጋ ኦሮሞ | ከፋሺስት ወረራ ወዲህ ዘመናዊ ጦር የማደራጀት ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱ |
| 12 | እስክንድር ደስታ | ሪር አድሚራል (ባህር ኃይል) | የንጉሠ ነገሥቱ የባህር ኃይል አዛዥ | የሸዋ አማራ | የንጉሠ ነገሥቱ የልጅ ልጅ |
| 13 | አሰፋ ደምሴ | ሌ/ጄኔራል | የንጉሠ ነገሥቱ የፕሮቶኮል ሹም | አማራ ኦሮሞ ድብልቅ | |
| 14. | ይልማ ሺበሺ | ሌ/ጄኔራል (ፓሊስ) | የንጉሠ ነገሥቱ የፓሊስ ሠራዊት ጠ/አዛዥ | ጉራጌና አማራ (ድብልቅ) | |
| 15. | በለጠ አበበ | ሌ/ጄኔራል | የድንበ ጠባቂ ጦር አዛዥ | የሸዋ አማራ | |
| 16. | ተሾመ እርገቱ | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የክፍለ ጦር አዛዥ | ጉራጌና ኦሮሞ (ድብልቅ) | ከ66 አብዮት በፊት በኤርትራ አማፂያን የተገደሉ |
| 17. | ጃጋማ ኬሎ | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የክፍለ ጦር አዛዥ | የሸዋ ኦሮሞ | 3000 አርበኞችን በመምራት የፋሺስት ጣልያን ወራሪዎችን የተጋፈጡ |
| 18. | ነጋ ኃይለሥላሴ | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ካቢኔ | የሸዋ አማራ | |
| 19. | ደበበ ኃይለማርያም | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘብ አዛዥ | የሸዋ አማራ | |
| 20 | አማን ሚካኤል አንዶም | ሌ/ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የኃይል አዛዥ | ኤርትራ | የ1950ቹ የሶማሊያ ጦር ጀግና፤ ለአጭር ጊዜ ርዕሰ ብሄር የነበሩ |
| 21. | አበበ ወልደ ሚካኤል | ሜጀር ጄኔራል | የፓሊስ አዛዥ | አማራ | |
| 22. | ደግነህ ጉግሳ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የኃይል አዛዥ | የወለጋ ኦሮሞ | |
| 23. | ሽፈራው ተሰማ | ሜጀር ጄኔራል | የምድር ጦር | አማራ | |
| 24 | ያዕቆብ ገብረ ልዑል | ሜጀር ጄኔራል | የምድር ጦር | ኤርትራ | |
| 25 | ታደሰ መልኬ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የገነት ጦር ማሰልጠኛ አዛዥ | የጎንደር አማራ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 26 | አበራ ወልደማርያም | ሜጀር ጄኔራል (አየር ኃይል) | የአየር ኃይል አዛዥ | ኦሮሞና አማራ ድብልቅ | |
| 27 | ታፈሰ ለማ | ሜጀር ጄኔራል | የኃይል አዛዥና የቤተመንግሥት ጥበቃ | አማራና ጉራጌ ድብልቅ | |
| 28 | ከበደ ወርቁ | ሜጀር ጄኔራል | የኃይል አዛዥ | የሸዋ አማራ | |
| 29 | ወልደፃድቅ ገበረመስቀል | ሜጀር ጄኔራል | የክብር ዘበኛ ም/ አዛዥ | ጉራጌ | |
| 30 | ጽጌ ገዝሙ | ሜጀር ጄኔራል | የመከላከያ በጀትና ፋይናንስ ኃላፊ | የሸዋ አማራ | |
| 31 | ጋሻው ከበደ | ሜጀር ጄኔራል | በኤርትራ የፖሊስ አዛዥ | አማራ | |
| 32 | አበበ ወልደማርያም | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የምድር ጦር | አማራ | |
| 33 | በረከት ገብረመድህን | ሜጀር ጄኔራል | የፓሊስ አዛዥ | ትግራይና ኤርትራ | |
| 34 | ቀልቤሳ ቤካ | ሜጀር ጄኔራል | የፓሊስ  አዛዥ | የወለጋ ኦሮሞ | |
| 35 | ግርማ ሙላት | ሜጀር ጄኔራል | የፓሊስ  አዛዥ | አማራ | |
| 36 | ከበደ ዋጋዬ | ሜጀር ጄኔራል | የክብርዘብ ም/ አዛዥ | የጎጃም አማራ | |
| 37 | አበበ ወልደሥላሴ | ሜጀር ጄኔራል | የፓሊስ አዛዥ | አማራ ሸዋ | |
| 38 | ስዩም ወልደጊዮርጊስ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የኃይል አዛዥ | አማራ ከሃረር | |
| 39 | ሞገስ በየነ | ሜጀር ጄኔራል | የፓሊስ አዛዥ | የሸዋ አማራ | |
| 40 | ግዛው በላይነህ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የኃይል አዛዥ | አማራ ከሃረር | በኋላ በደርግ ቺፍ አፍስታፍ የሆኑ |
| 41 | መርዕድ ግዛው | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የኃይል አዛዥ | የሸዋ አማራ | |
| 42 | ታደሰ ገብሬ | ሜጀር ጄኔራል | የፓሊስ አዛዥ | አማራ | |
| 43 | ዋቅጅራ ሳርዳ | ሜጀር ጄኔራል | የኃይል አዛዥ | የወለጋ ኦሮሞ | |
| 44 | ነጋ ተገኝ | ሜጀር ጄኔራል (ጦር ሠራዊት) | የኃይል አዛዥ | የጎንደር አማራ | |
| 45 | ተድላ መኮንን | ሜጀር ጄኔራል | የምድር ጦር ም/አዛዥ | የሸዋ አማራ | |